በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/...1048.../18

ቀን፡-13.../05/2018 ዓ/ም

ለአብክመ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፡ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዲስ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው በመላክ እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስራና ስልጠና ቢሮ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ 18/2015 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 18/2015 ዓ/ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 39/2018 ዓ.ም አድርጎ የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 25 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

GE

ገረመው እሸቱ

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትህ ቢሮ

# በአ.ብ.ክ.መ.ሥራና
# ስልጠና ቢሮ

# የገጠር ቀበሌ ሥራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የዝውውር መመሪያ

## ቁጥር 39

ነሀሴ 2015 ዓ/ም
ባህር ዳር

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስራና ስልጠና ቢሮ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 39/2018

መግቢያ

የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበርና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተዋረድ ከተቋቋሙት የዞንና የወረዳ ስራና ስልጠና ጽ/ቤት አደረጃጀቶች በተጨማሪ በቀበሌ ደረጃ የስራ እድል ፈጠራን ለማሳለጥ እና ለማስፈጸም ይረዳ ዘንድ በክልላችን የገጠር ቀበሌዎች ላይ የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ተመድበው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች በየተመደቡበት ቀበሌ ተግባርና ኃላፊነታቸዉን በተነሳሽነትና በዉጤታማነት እንዲያከናዉኑ ለማድረግና የዝዉዉር መመሪያ አለመኖር ምክንያት እያጋጠማቸዉ ያለዉን የመልካም አስተዳደር ችግሮች መፍታት ያስፈልጋል።

በመሆኑም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የዝውውር መመሪያ አዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራጥናት ባለሙያዎች የዝውውር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 39/2018 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ዝውውር መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"ቢሮ"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 280/2014 መሰረት የተቋቋመ የስራና ስልጠና ቢሮ ማለት ነዉ፡፡

2/ **"ኮሚሽን"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 280/2014 መሰረት የተቋቋመ የሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ኮሚሽን ማለት ነዉ፡፡

3/ **"መምሪያ"** ማለት በየደረጃው የተቋቋመ የስራና ስልጠና መምሪያ ወይም የሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ ማለት ነዉ፡፡

4/ **"ጽ/ቤት"** ማለት በየደረጃው የተቋቋመ የስራና ስልጠና ጽ/ቤት ወይም የሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡

5/ **"የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ"** በቀበሌ ደረጃ የስራ አጥነት ችግርን ለመቀነስ በተመደበበት ቀበሌ ዉስጥ የስራ አማራጮችን በጥናት በመለየት ፣ ባለ ድርሻ አካላትን በማስተባበር ዘላቂ የስራ ዕድል ለመፍጠር የሚሰራና ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ ማለት ነዉ፡፡

6/ **"የስራ ልምድ"** ማለት ህጋዊ እውቅና ካላቸው የግል፣ መንግስታዊ ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና አለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ በየ ወሩ ቋሚ ደመወዝ እና የስራ ግብር የተከፈለበት፣ ስራውን ለሚያሰራው መ/ቤት በመደበኛ ስራ ስዓት የተወሰነ ስራ በማከናወን የተገኘ የስራ ልምድ ወይም ችሎታ ማለት ነው ፡፡

7/ **"የጋብቻ ማስረጃ"** ማለት በማዘጋጃ ቤት ወይም በወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ወይም በሃይማኖት ተቋም ወይም በባህላዊ ጋብቻ የሚፈፀምና የሚቀርብ የጋብቻ ማስረጃ ነዉ፡፡

8/ "ዝውውር" ማለት አንድ የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ከሚሰራበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ወደ ሌላ ወረዳ ወይም ዞን አዛውሮ መመደብ ማለት ነው ፡፡

9/ "የህክምና ቦርድ ማስረጃ" ማለት ለቦታ ዝውውር የሚያበቃ ህጋዊ ማስረጃ ሆኖ ከመንግስት ሪፈራል /ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በሀኪሞች ቦርድ የሚሰጥ የህክምና ማስረጃ ነው ፡፡

10/ "ምደባ" ማለት የገጠር የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ በመንግሥት ወጭ ትምህርቱን አሻሽሎ ሲመለስ፣ በጤና ችግር እና በህይወት የመኖር የደህንነት ስጋት ምክንያት ከመደበኛ ዝዉዉር ዉጭ የሚቀጠሩ አዲስ ባለሙያዎች የመደበኛ ዝዉዉር እስኪፈፀም ድርስ የሚሰጥ ጊዚያዊ የቀበሌ ምደባ መስጠት ነዉ ፡፡

11/ "የቀበሌ ምድብ ደረጃ" ማለት በአየር ጠባይ ተስማሚነት ደረጃ፣ በመሠረተ ልማት አቅርቦት ፣ ከወረዳው ርዕሰ ከተማ ያለው ርቀትና በሌሎችም መስፈርቶች ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የምድብ የስራ ቦታ ቀበሌ ለኑሮ የምቹነት ደረጃ ማለት ነው ፡፡

12/"አካል ጉዳተኛ" ማለት በሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት በሰዉ ኃይል ስምሪት ፣ ምልመላና መረጣ በተሰጠዉ ትርጓሜ መሰረት የተቀመጠዉን ትርጓሜ ማለት ነዉ፡፡

13/ "የደህንነት ስጋት" ማለት በስራ አካባቢ ተረጋግቶ ስራን ለመስራት የማያስችልና በህይወት የመኖር ስጋት ነው ፡፡

14/ "የህግ ከለላ የሚያስፈልጋቸው" ማለት የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 መሰረት በጠቋሚ ወይም በምስክር ወንጀል ምርመራ፣በወንጀል ክስ ወይም በወንጀል ማጣራት ሒደት መረጃ ወይም ምስክርነት የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ ነው ፡፡

15/ "የገጠር ቀበሌ" ማለት በገጠር ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ስር የታቀፉ የገጠር ቀበሌዎች ናቸው፡፡

## 3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀዉ ሁሉ ሴትንም ይጨምራል ፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በክልሉ ዉስጥ በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ተመድበው በሚሰሩ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡

# ክፍል ሁለት

## የባለሙያዎች መደበኛ ዝውውር

### 5. የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች መደበኛ ዝዉዉር ከመፈፀሙ በፊት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

1/ በየአመቱ በሚደረግ ዝዉዉር አንድ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ካለበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመዛወር ባለበት ቀበሌ ቢያንስ ሁለት አመት ማገልገል ይኖርበታል።

2/ አንድ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ መደበኛ ዝውውር ከተጠናቀቀ በኋላ በቅጥር፤ በትምህርት ማሻሻል ወይም በዝውውር ከሌላ ወረዳ ወይም ዞን ከመጣ በወረዳው ውስጥ ባሉት ክፍት ቀበሌዎች በጊዜያዊነት ተመድቦ እንዲሰራ ይደረጋል። ክፍት ቀበሌ ሳይኖር የስምሪት ወይም ምደባን ወይም ዝዉዉርን ጥያቄን መቀበል አይቻልም ።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ አንድ የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ በጊዜያዊነት ከተመደበ መደበኛ ዝውውር እስከ ሚሰራ ድረስ በተመደበበት ቀበሌ እንዲቆይ ይደረጋል ። በጊዚያዊነት የተመደበ ሙያተኛ መደበኛ ዝውውር በሚፈጸምበት ጊዜ ሁለት ዓመት መጠበቅ ሳያስፈልግ የሚፈልጋቸዉን ሶስት (3) ቀበሌዎች በቅደም ተከተል መሙላት አለበት። በነበረበትም ሆነ አዲስ በመረጣቸዉ ቀበሌዎች ተወዳድሮ ከተሸነፈ ወይም ካልመረጠ በቀሪ ክፍት ቀበሌ በቋሚነት እንዲመደብ ይደረጋል ። በጊዜያዊነት ተመድበው የነበረ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች በምደባ ወቅት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ ከሆኑ ባላቸው ጠቅላላ አገልግሎት ቅደም ተከተል መሰረት እንዲመደቡ ይደረጋል ። አገልግሎታቸዉ እኩል ከሆነ ቅድሚያ ለአካል ጉዳተኛ ይሰጣል፣ አካል ጉዳተኞች ቁጥራቸዉ ከአንድ በላይ ከሆኑ በሲቪል ሰርቪስ እና የሰዉ ሃብት ልማት ኮሚሽን በተቀመጠዉ የስምሪት፣ ምልመላና መረጣ መመሪያ መሰረት ቅድሚያ ለሚሰጠዉ የጉዳት አይነት ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን የጉዳት ሁኔታቸዉ ተመሳሳይ ከሆነ ግን በእጣ ይለያሉ ። ከተወዳደሪዎቹ ዉስጥ አካል ጉዳተኛ ከሌለ ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል። ተመሳሳይ ጾታ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ ።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተገለጸው መሰረት በቋሚነት የሚመደብ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ በወረዳው ሁለት አመት እስካገለገለ ድረስ በቀጣይ በሚደረገዉ ዝውውር በአንድ ቀበሌ ሁለት አመት የመቆየት ግዴታ የለበትም።

5/ አንድ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ በሚሰራበት ወረዳ ዉስጥ ባሉ ቀበሌዎች ለመዛወር ፍላጎት ያለዉ ከሆነ የሚፈልጋቸዉን ቀበሌዎች ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ በደረጃ ያስቀምጣል፡፡ ከአንድ ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ባሉ ቀበሌዎች ለመዛወር ከሆነ የሚፈልገዉን ወረዳዎች ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ በደረጃ ያስቀምጣል፣ ከዞን ወደ ዞን ለመዛወር ፍላጎት ያለዉ ከሆነ ሶስት ዞኖችን ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ በደረጃ በማስቀመጥ እና በመረጣቸዉ ዞኖችም ዉስጥ ሶስት ወረዳዎችን በደረጃ በመዘርዘር ለዚሁ አላማ በተዘጋጀው የመጠየቂያ ፎርም ሞልቶ በወቅቱ ለወረዳ ሥራና ስልጠና ጽ/ቤት እና ለሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተገለጸው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከወረዳው ውጪ በዝውውር ወቅት የሚመጣ ባለሙያ በወረዳው ውስጥ ባሉ ክፍት ቀበሌዎች በወረዳው ውስጥ ካሉ ቀበሌውን ከሞሉት ሙያተኞች ጋር በመወዳደር የሚመደብ ይሆናል ፡፡ ሆኖም ግን አንድ በወረዳዉ ዉስጥ የቆየ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ የዝውውር ፍላጎቱን በደረጃ ዘርዝሮ ካቀረባቸው ቀበሌዎች በውጤቱ ምክንያት ማግኘት ባይችል በነበረበት ቀበሌ ይቆያል፡፡ ከሌላ ዞን ወይም ወረዳ የመጣ ከሆነ ተወዳድሮ ከተሸነፈ ክፍት በሚሆኑ ቀበሌዎች ይመደባል፡፡

7/ ተመሳሳይ ፆታ ያላቸዉ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች በቀበሌዉ ወይም በወረዳዉ መቆየት የሚገባቸዉን የአገልግሎት ጊዜ አሟልተዉ ሲወዳደሩ (የሁለት ዓመት በስራ ላይ ቆይታ) እኩል ነጥብ ኑሯቸዉ በተመሳሳይ አንድ ቀበሌ ቢመርጡ ቅድሚያ የሚሰጠዉ የተሻለ የስራ አፈፃፀም ዉጤት ላለዉ ይሆናል፡፡ ዉጤቱም በቅርብ ጊዜ የተሞላለት ሆኖ የአራት ተከታታይ ጊዜያት አማካይ የስራ አፈጻጸም ዉጤት የሚያዝ ሲሆን የስራና ስልጠና ጽ/ቤት ኃላፊ ያመነበት በስራ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት በአሳማኝ ምክንያት የአንድ አመት የስራ አፈጻጸም ብቻ የተሞላለት ከሆነ የአንድ አመቱን አማካይ ዉጤት የሚያዝለት ይሆናል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል የስራ አፈጻጸም ዉጤት ወይም ነጥብ ካመጡ ቅድሚያ ለአካል ጉዳተኛ የሚሰጥ ሆኖ የአካል ጉዳተኞቹ ከአንድ በላይ ከሆኑ በንዑስ አንቀጽ 5 “ሐ” አግባብ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡ ከተወዳደሪዎቹ ዉስጥ የአካል ጉዳተኛ ከሌለ ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤ ተመሳሳይ ጾታ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ፡፡

9/ አንድ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ አስቀድሞ የዝውውር ፍላጎቱን ካሳወቀ በኂላ ካለበት ቀበሌ መዛወር ካልፈለገ ዝዉዉር ከመሰራቱ በፊት በማመልከቻ ለወረዳው ሥራና ስልጠና ጽ/ቤት እና ለወረዳዉ የሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት ፡፡ ይሁን እንጅ ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ባለበት እንዲቆይ ከተደረገ ሌላ ዝውውር ሲታይለት

የሚችለው ከአንድ አመት ቆይታ በኋላ በመደበኛ ዝዉዉር ወቅት ይሆናል፡፡ የሚያዝለት የስራ አፈጻጸም ዉጤትም የቅርብ ጊዜ የአራት ተከታታይ አማካይ ውጤት ይሆናል፡፡

10/ በየሁለት አመቱ በወረዳው ያሉ የገጠር ቀበሌዎች ወይም የወረዳዎች ወይም ዞኖች ባላቸው የስራ አመችነት፣ የገጠር መሰረተ ልማት መስፋፋት፣ የአየር ንብረት ሁኔታ እና ከወረዳ ማዕከል ያለዉ እርቀት ግምት ዉስጥ በማስገባት በወረዳው ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ቀበሌዎች ከፍተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ፣ መካካለኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ እና ዝቅተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ በሚል ከተሻለው ጀምሮ በስራና ስልጠና ጽ/ቤት እና ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት በኩል ለአስተዳደር ምክር ቤት በደረጃ ለይቶ ያጸድቃል፡፡

## 6. ዝውውር ሲፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1/ የወረዳው ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ኃብት ልማት ጽ/ቤት የዝውውር ማስታወቂያዉ ለሁሉም የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ባሉበት ቀበሌ በመለጠፍ እና ከተቻለ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ዝውውር የሚፈልጉ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎችን እንዲመዘገቡ ወይም የዝዉዉር ፎርም ሞልተዉ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ በተቀመጠዉ ጊዜ ያልተመዘገበ ለዝዉዉር አይቀርብም፡፡

2/ የዝዉዉር ስራ ከመጀመሩ በፊት የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የዝውውር መጠየቂያ ፎርም በተቀመጠዉ ጊዜና በአግባቡ ተሞልቶ የቀረበ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል ፡፡

3/ በወረዳው ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት አማካኝነት ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የዝውውር መጠየቂያ ፎርም ወይም መረጃ አሰባስቦና አጠናቅሮ ካጠናቀቀ በኃላ ስለ ትክክለኛነቱ ለማረጋገጥ የተጠናቀረዉን መረጃ ግልጽ በሆነ ቦታ መለጠፍ እና ከተቻለ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመለጠፍ ለዝዉዉር አመልካቾች ማሳወቅ ይኖርበታል ፡፡

4/ የዝውውር ዝርዝር መረጃ የደረሰው የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ዝርዝሩን አይቶ የመረጃ ስህተት ያጋጠመው ከሆነ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በማመልከቻ የማስተካከያ ጥያቄ (ቅሬታ) ማቅረብ አለበት ፡፡ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረበ የመረጃውን ትክክለኛነት እንዳመነበት ተቆጥሮ መረጃው ለዝውውር አገልግሎት ይውላል፡፡

5/ የመረጃ ስህተት ቅሬታ የደረሰው የወረዳ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ጽ/ቤት ቅሬታውን በአግባቡ ተመልክቶና የቀረበውን የዝውውር መጠየቂያ ፎርም በማገናዘብ ለዝዉዉር

ስራ ምቹ ያደርጋል ፡፡ በጽ/ቤት ደረጃ የተጠናቀረዉ መረጃ ለዞን ስራና ስልጠና መምሪያ እና ለሲቭል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ መድረስ ይኖርበታል ፡፡ የዞኑ ስራና ስልጠና መምሪያ ከወረዳ የደረሰዉን የዝዉዉር መረጃ አደራጅቶ እና አጠናቅሮ ለክልል ስራና ስልጠና ቢሮ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ መላክ ይኖርበታል፡፡

6/ የክልሉ ሥራና ስልጠና ቢሮ ከዞን ስራና ስልጠና መምሪያ የደረሰዉን የተሟላ የዝዉዉር መረጃ በሶስት ቀናት ዉስጥ በማደራጀት ለዝዉዉር ሥራዉ ዝግጁ ካደርገ በኋላ በአምስት ቀናት ዉስጥ የዞን ዞን ዝዉዉር በማጠናቀቅ ውጤቱን ለዞኖች በደብዳቤ እንዲደርስ ያደርጋል ፡፡ በተሰራዉ ዝዉዉር ቅሬታ ካለ በ5 ተከታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ በማደራጀት ለቢሮዉ መቅረብ ይኖርበታል ፡፡ ቢሮዉ የቀረበለትን ቅሬታ በሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ አጣርቶ የመጨረሻ ምላሽ ይሰጣል ፡፡ ከዞን ዞን ዝዉዉር ለተሰራላቸዉ ሙያተኞች በክልሉ የሥራና ስልጠና ቢሮ የሰዉ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል ወደ ዞን የተዛወሩ መሆኑን ደብዳቤ እንዲደርሳቸዉ ይደርጋል ፡፡

7/ ቅሬታዉ በክልል ደረጃ መልስ ካገኘና ከተጠናቀቀ በኋላ በዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ ከሥራና ስልጠና መምሪያ ጋር በክልል ደረጃ በሥራና ስልጠና ቢሮ የተሰራዉን ዝዉዉርና ከወረዳዎች ለወረዳ ወረዳ ዝዉዉር ተሞልቶ የመጣዉን መረጃ በመያዝ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ የወረዳ ወረዳ ዝዉዉር ሰርቶ በማጠናቀቅ ለወረዳዎች በደብዳቤ ያሳዉቃል፡፡

8/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 6 "ሠ" የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዞን ደረጃ በተሰራዉ የወረዳ ወረዳ ዝዉዉር ቅሬታ ካለ በ5 ተከታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ በማደራጀት ለሲቭል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ ማሳወቅ አለባቸዉ ፡፡ መምሪያዉም የቀረበለትን ቅሬታ በሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ አጣርቶና አስተካክሎ የመጨረሻ ምላሽ ይሰጣል ፡፡ ከወረዳ ወረዳ ዝዉዉር ለተሰራላቸዉ ሙያተኞች በዞኑ የሥራና ስልጠና መምሪያ ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ በማጸደቅ በዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ በኩል ዝርዝራቸዉን ለወረዳ በህጋዊ በደብዳቤ እንዲደርሳቸዉ ያደርጋል፡፡

9/ ከላይ በንዕስ አንቀጽ 6 "ሸ" የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዞን ደረጃ የቅሬታ ስርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በወረዳ/ከተማ አስተዳደር የሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት በኩል የሥራና ስልጠና ጽ/ቤትን ባሳተፈ መልኩ በዞን ደረጃ የተሰራዉን ወይም የጸደቀዉን ዝዉዉርና ከቀበሌ ቀበሌ ለመዛወር ተሞልቶ የመጣዉን መረጃ በመያዝ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ

የቀበሌ ቀበሌ ዝዉዉር በመስራትና በስራና ስልጠና ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ በማጸደቅ ለተዛወሩ ሙያተኞች ግልጽና ተደራሽ በሆነ ቦታ በመለጠፍ ወይም ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በማሳወቅ በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ቅሬታ እንዲያቀርቡ ይደረጋል። የቅሬታዉ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኃላ በሁለት ተከታታይ ቀናት በማጣራት የመጨረሻ ዉሳኔ ወይም ዉጤት በደብዳቤ ለእያንዳንዱ የዝዉዉር ተጠቃሚ ሙያተኛ እንዲደርሰዉ ይደረጋል ።

10/ የዝውውር እድል ተጠቃሚ የሆነና ስለ መዛወሩ ደብዳቤ የደረሰዉ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ዝዉዉር በተሰራበት ዓመተ ምህርት ከሰኔ ሃያ አምስት እስከ ሰላሳ ባሉት ቀናት ዉስጥ በነበረበት ቀበሌ ያሉ ህጋዊ ሰነዶችና ዝርዝር መረጃዎችን ፣ የተጠናቀቁና በሂደት ላይ ያሉ ስራዎችን፣ ፋይሎችን፣ ማንዋሎችን እና ንብረቶችን በቃለ ርክክብ በመፈጸም፣ ክሪላንስ በመያዝና ለወረዳ ስራና ስልጠና ጽ/ቤት በማሳወቅ ከሀምሌ አንድ ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ አዲስ በተመደበበት ቀበሌ መደበኛ ሥራዉን መጀመር ይኖርበታል።

11/ የሥራና ስልጠና ጽ/ቤት የተዛወሩ የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎችን የዝውውር ደብዳቤ እንዲደርሳቸውና የርክክብ ስርአቱ በአግባቡ መፈጸሙን ይከታተላል። የቀበሌ አስተዳዳሪዉ የተዛወረዉ ሙያተኛ ስራ የጀመረ መሆኑን ለስራና ስልጠና ጽ/ቤት በደብዳቤ እንዲያረጋግጥ ይደረጋል።

## 7. <u>በዝውውር ወቅት የጋብቻ ሁኔታ የሚታይበት አግባብ</u>

1/ የጋብቻ ማስረጃ የመደበኛ ዝውውር ከሞሞላቱ ከስድስት ወራት በፊት ከዝውውር ተጠቃሚዎች ከግል ማህደራቸው ጋር ተያይዞ መገኘት አለበት።

2/ የጋብቻ ማስረጃው ተቀባይነት የሚኖረው ከማዘጋጃ ቤት ወይም በወሳኝኩነቶች ወይም በሀይማኖታዊ ስነ-ስርዓት ወይም በባህላዊ ጋብቻየ ተፈጸመ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው።

3/ ትዳርን መሰረት ያደረገ ዝውውር የሚፈፀመው የባልና ሚስት አገልግሎት ተደምሮና አማካይ ዉጤቱ ተወስዶ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች በነጥብ በልጠው ሲገኙ ሲሆን የሚቀርበው የአገልግሎት ማስረጃም ከተሰጠ 3 ወርና በላይ ያልሆነው ሆኖ ዝውውር ሲሞላ አብሮ መቅረብ አለበት ።

የባልና የሚስት አገልግሎት ተደምሮ ለሁለት ተካፍሎ የሚገኘዉ አገልግሎት ከዝዉዉር ጠያቂዉ የተናጠል አገልግሎት የሚያንስ ከሆነ የራሱ አገልግሎት ብቻ ይያዝለታል። የትዳር አጋሩ የመንግስት ሰራተኛ ባትሆንም በአንድ ላይ ለመኖር የጋብቻ ማስረጃ ካያዙ በምትኖርበት

ቀበሌ የኗሪነት ማስረጃ በማቅረብ በተቀመጠዉ አሰራር ለማቀራረብ ታሳቢ ተደረጎ ይሰራል፡፡ የባለ ትዳሮች ነጥብ ከሌሎች ትዳር ወይምጋብቻ ከሌላቸዉ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች እኩል ከመጣ ለባለትዳሮች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

4/ ባለ ትዳሮች ዝውውር የሚጠይቁት ለመቀራረብ እስከ ሆነ ድረስ ባለ ትዳሮችን የማቀራረብ ሁኔታ በዝውውር ወቅት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህም ማለት በመደበኛ ዝውውር ወቅት በተቀመጠዉ የዝዉዉር መስፍርት ተወዳድረዉ መቀራረብ ባይችሉ ባለሙያ ያልተመደበበት ክፍት ቀበሌ ካለ እና ካመለከቱ ዝዉዉሩ ይፈጸማል፡፡

5/ በተለያዩ ሁለት የገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩ ባለትዳር የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ወደ አንዳቸው አቅራቢያ ቀበሌ ለመዛወር ሁለቱም በዝውውር መጠየቂያ ፎርም ላይ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

6/ ባለ ትዳሮች ዝውውር የሚጠይቁት ለመቀራረብ እስከ ሆነ ድረስ ባለትዳሮቹ በአንድ ወረዳ ስር ባይሆኑም የምትመርጠው ቀበሌ ወደ አጐራባች ወረዳ ቀበሌ የሚቀርብ ከሆነ እና የዝዉዉር ተጠቃሚዉ ፍላጎት ካሳየ ለጋብቻ የሚሰጠው ነጥብ በመጠቀም ተጠቃሚ ይሆናል ፡፡

7/ ባለበት ቀበሌ የትዳር ጓደኛ ያለዉ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ወረዳ ወይም ዞን የመዛወር ፍላጎት ካለዉ ዝዉዉር ለመሙላት ባለቤቱ በሚሞላዉ ዝዉዉር የምትስማማ መሆኑን በደብዳቤ በአካልና በፊርማ በማረጋገጥ ለሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት እና ለስራና ስልጠና ጽ/ቤት ማቅረብ ይገባል፡፡

## 8. የዝውውር ማወዳደሪያ መስፈርቶች

1/ ከ100 የሚሰጥ ነጥብ

ሀ) የስራ አፈጻጸም ውጤት............ 50%

በውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት መሰረት በያንስ የ4 ጊዜ ተከታታይ የስራ አፈጻጸም አማካይ ነጥብ ከ50% ይያዛል፡፡ ይህም የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎችን በቀጣይ የበለጠ ለስራ እንዲነሳሱና ውጤታማ እንዲሆኑ ከማስቻሉም በላይ ጤናማ የሆነ የውድድር መንፈስ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም አንድ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ በተመደበበት ቀበሌ በተጨባጭ ያመጣው ለውጥ መነሻ ተደርጐ የተሰጠው የ2 ዓመት የስራ አፈጻጸም አማካይ ውጤት ከ50% ይያዛል፡፡ የስራ አፈጻጸም ውጤቱም በ0.50 ተባዝቶ ይቀመጥለታል፡፡ ይህም ማለት የ4 ጊዜ ተከታታይ አማካይ ውጤት 80% ላመጣ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ 80x0.50=40% ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡ ሆኖም የ4 ጊዜ ተከታታይ የስራ አፈጻጸም

የሌለው በሚያቀርቡት አሳማኝ ምክንያት የ2 ጊዜ የስራ አፈጻጸም ዉጤት ተይዞላቸው እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

ለ) የስራ ልምድ/አገልግሎት ዘመን/... 25%

የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ለመስሪያቤቱ ወይም ለሀገሩ በሰጠው የአገልግሎት ዘመን ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ በየትኛውም ቦታና በማንኛውም የስራ መስክ የሰራበትና በህጋዊ የስራ ልምድ 25 ዓመትና በላይ የአገልግሎት ላላቸው 25% የሚሰጥ ሲሆን ከ25 አመት በታች አገልግሎት ላላቸዉ በአገልግሎት ዘመናቸው ተሰልቶ የሚመጣው ውጤት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ 20 ዓመት አገልግሎት ያለዉ ዝቋላ ወረዳ የስራ ሰራተኛ 20x 1.5 + 20 X 25 = 50 ስለዚህ ለግለሰቡ 25% ዉጤት ያገኛል ማለት ነዉ፡፡

ሐ) የግለሰቡ የማህደር ጥራት........... 5%

ለማህደር ጥራት የሚያዘው የሚሰጠው ነጥብ ሰኔ 2013 ዓ/ም በተሸሻለዉ ምልመላና መረጣ መመሪያ አንቀጽ 4.4.2 (ለ) በተገለጸዉ ሰንጠረዝ መሰረት ይሆናል፡፡

መ) የጋብቻ ሁኔታ ......................... 5%

ባለትዳሮች ለዝውውር የሚያቀርቡት የጋብቻ ማስረጃ በዝውውር ፈላጊዎች የግል ማህደር ላይ 6 ወርና በላይ የተያያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሠ) የስራ ቦታ አስቸጋሪነት............ 15%

በየሁለት ዓመቱ የሚሰራው ዝውውር በወረዳው ውስጥ ያሉ ቀበሌዎችን ባላቸው የስራ አመችነት፣ የገጠር መሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የአየር ንብረት ሁኔታ፣ ከወረዳዉ ማዕከል ካላቸው ርቀትና ሌሎች ሁኔታዎችን በማየት ሁሉንም ቀበሌዎች እንደ ወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ በ3 ደረጃ ተፈርጀው ለወረዳ /ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በማቅረብ ደረጃው እየተወሰነ በቅደም ተከተል በሚሰጣቸው የፍረጃ ነጥብ መሰረት ከቀበሌ ቀበሌ ዝውውር የሚሰራ ሲሆን፡-

1) ከፍተኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ቀበሌ ................... 15%

2) መካከለኛ ደረጃ ለኑሮ አስቸጋሪ ቀበሌ .................10%

3) ዝቅተኛ ደረጃ ለኖሮ አስቸጋሪ ቀበሌ ................... 5%

የወረዳዉ አስተዳደር ም/ቤት የቀበሌዎችን ሁኔታ ከላይ በተቀመጠዉ በ3 ደረጃ አስቀምጦ ተፈጻሚ እንዲሆን ለወረዳው ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ያስተላልፋል።

2/ በልዩ ድጋፍ የሚሰጥ ነጥብ (ተጨማሪ)

ሀ) ለሴቶች ................................ 3%

ለ) ሴት አካል ጉዳተኛ ከሆነች ለሴት የሚሰጠው 3 ነጥብ ቀርቶ....... 5%

ሐ) ለወንድ አካል ጉዳተኞች ............... 4%

## 9. እርስ በእርስ ዝውውር

1/ ተመሳሳይ የካርየር ደረጃና ደመዎዝ ያላቸው የገጠርቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች እርስ በእርስ ለመዛወር ከፈለጉና አሰሪ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በዝውውሩ ከተስማሙ መዛወር ይችላሉ።

2/ የእርስ በዕርስ ዝውውሩ ከቀበሌ ቀበሌ ከሆነ በስራና ስልጠና ጽ/ቤት በኩል፣ ከወረዳ ወረዳ ከሆነ በስራና ስልጠና መምሪያ በኩል፣ ከዞን ዞን ከሆነ በክልል ስራና ስልጠና ቢሮ በኩል ዝውውሩ የሚፈፀም ይሆናል።

3/ ከላይ በን/አንቀጽ 9 "ሀ" የተገለፀው ቢኖርም በካርየር ደረጃቸው ተመሣሣይ ሆኖ እስከ ሦስት እርከን የደመወዝ ልዩነት ቢኖርም ላኪና ተቀባይ መ/ቤቶች ከተስማሙ ዝውውሩን ማከናወን ይቻላል ።

## 10. በመደበኛ ዝውውር ወቅት የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚዎች

1/ ከመንግስት ሪፈራል /ስፔሻላይዝድ/ ሆስፒታሎች በቀረበ የህክምና ቦርድ ማስረጃ የሚያቀርቡ ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የሚያቀርቡት የህክምና ማስረጃ ከህክምና ማስረጃ አቀራረብ መመሪያ መሰረት ያደረገና በትክክለኛ የህክምና ማስረጃ ስለመሆኑ በሚሰሩበት የአስተዳደር ዕርከን እናት መ/ቤታቸው አማካኝነት እየተረጋገጠ የሚቀርብ ሆኖ የህክምና ማስረጃው ሠራተኛው በበሽታው ምክንያት አሁን በሚሰራበት ቦታ ላይ ለመስራት የማይችልበት ሁኔታና መሰል ጉዳዮችን በዝርዝር የሚገልጽ ሆኖ የህክምና ማስረጃው ከተሰጠ አንድ ዓመት ያልበለጠው /የታደሰ / ሆኖ በቅድሚያ በእናት መስሪያ ቤቱ አማካኝነት ለጤና ተስማሚ የሆነ የስራ ምደባ እንዲሰጠው ይደረጋል። በእናት መስሪያ ቤቱ በኩል የጤና ችግሩ የማይፈታለት ከሆነ ለዞን፣ሪጆፖሊታን ሲቪል ስርቪስ መምሪያና ለወረዳ፣ከ/አስተዳደር ሲቪል ስርቪስ ጽ/ቤት ሲቀርብ በመደበኛ ዝውውር ውድድር፤-

ሀ) በጤና ችግር ምክንያት ከመንግሥት ሪፈራል/ ስፔሻላይዝድ/ ሆስፒታል በሀኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ማስረጃ የኩላሊት እጥበት የሚደረግላቸው ህሙማን፣ የካንሰር፣የልብ ህሙማን፣ የአዕምሮ እና ኤችአይ ቪኤድስ ህሙማን ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የሚያቀርቡ ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ከማንኛውም ዝውውር ፈላጊ በፊት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ። ይሁን እንጅ የተለያየ ፆታ ያለቸው ከሆኑ ቅድሚያ ለሴቶች ይሰጣል።

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" ከተገለፁት ውስጥ ለህመምተኛ አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ፤ለህመምተኛ አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለህመምተኛ ባለትዳሮች ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ፣ህመምተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለህመምተኛ አካል ጉዳተኛ ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ ። ይሁንጅ እንጅ የተለያየ ፆታ ያለቸው ከሆኑ ቅድሚያ ለሴቶች ይሰጣል።

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የተገለፁት ከተስተናገዱ በኂላ ወይም በሌሉበት ሁኔታ በሌሎች በሽታዎች ምክንያት በጤና ችግር ከመንግሥትሪፈራል/ ስፔሻላይዝድ/ ሆስፒታል በሀኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ህሙማን ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የሚያቀርቡ ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ። ይህም ሆኖ ከዝውውር ፈላጊዎች መካከል አካል ጉዳተኛ ባለ ትዳር ካለ ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ።አካል ጉዳተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለህመምተኛ ባለትዳር ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ ። ህመምተኛ ባለትዳር ከሌሉ ለአካል ጉዳተኛ ቅድሚያ ይሰጣል ከአንድ በላይ ከሆኑ በእጣ ይለያሉ ። ይሁን እንጅ የተለያየ ፆታ ያለቸው ከሆኑ ቅድሚያ ለሴቶች ይሰጣል።

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሐ" የተገለፀው ቢኖርም ሊዛወሩ የሚችሉበት ተመሳሳይ የሥራ መደብ ባለመገኘቱ ለጊዜው ከተሰጣቸው የህክምና ቦርድ ማስረጃ አንፃር ችግራቸው ያልተቀረፈላቸው ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የተሰጣቸው የህክምና ማስረጃ የታደሰና ዘላቂነት ያለው ከሆነ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅማችሁበታል በሚል ቀጣይ ዝውውር በሚፈፀምበት ጊዜ ሊታገዱ አይገባም።

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሐ" የተገለጹት ዝውውር ጠያቂዎች በሌሉበት ሁኔታ ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ ይሰጣል። ይሁን እንጅ የተለያየ ፆታ ያለቸው ከሆኑ ቅድሚያ ለሴቶች ይሰጣል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "መ" የተገለጹት ዝውውር ጠያቂዎች በሌሉበት ሁኔታ በህይወት ለመኖር የደህንነት ስጋት የሚያጋጥማቸው ሰራተኞች በሚሰሩበት

ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ዋና አስተዳደሪ /ከንቲባ ለግለሰቡ የሚሰጠው ማስረጃ ከቦታው ካልተነሳ ለህይወቱ አስጊ የሆነና ልንከላከልለት የማንችል መሆኑን በማለት ማስረጃ ሲሰጥ እና በየደረጃው ከሚገኝ ፖሊስ እና ፍትህ ተቋም የመዝገብ ቁጥሩና መዝገቡ የተከፈተበት ጉዳይ በዝርዝር የሚያሳይ የተጣራና የተረጋገጠ ማስረጃ እንዲሁም የዝምድናውን አይነት የሚገልፅ ማስረጃ ከፍርድ ቤት ማቅረብ እና በየደረጃው ያለው ሲቪል ሰርቪስ ተቋም የተሰጠው ማስረጃ በትክክለኛ ችግሩ የገጠመው መሆኑን በማረጋገጠ ማስረጃ ሲያቀርቡ በመደበኛ ዝውውር ወቅት ከሌሎች የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚዎች ከተስተናገዱ በኂላ የቅድሚያ ዕድል ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ዝውውሩ የሚከናወነው የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ሲሰሩ ከነበሩበት ቀበሌ ጋር ተመሳሳይ በሆነ የቀበሌ የቦታ ምድብ ደረጃ መሰረት ዝውውሩ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡

## 11. <u>የዝውውር ምደባ ተጠቃሚዎች</u>

1/ የወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 በተገለፀው መሰረት የህግ ከለላ የሚያስፈልጋቸው የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ከፌደራል ፍትህ ሚኒስተር ሚኒስትር/ሚኒስትር ዴኤታ ወይም ከክልል ፍትህ ቢሮ በኃላፊ/ም/ኃላፊ የተፈረመ ሆኖ የመዝገብ ቁጥሩና መዝገቡ የተከፈተበት ጉዳይ በዝርዝር የሚያሳይ የተጣራና የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች በአንድ ወረዳ ውስጥ ከሚሰሩበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ በወረዳ ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ፣በአንድ ዞን ከሚሰሩበት ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር ወደ ሌላ ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ከሚሰሩበት ከተማ አስተዳደር ወደ ሌላ ከተማ አስተዳደር /ወረዳ በዞን ሲቪል ሰርቪስ መምሪያ በኩል፣ ከአንድ ዞን/ሬጆፖሊታን ከተማ ወደ ሌላ ዞን/ሬጆፖሊታን ከተማ የሚደረግ ምደባ ግን በክልሉ ስራ ስልጠና ቢሮ በኩል በጀት ያለው ክፍት የስራ መደብ እስከተገኘ ድረስ የያዙትን ደመወዝና ደረጃ እንደያዙ በተመሳሳይ የቀበሌ የስራ ምድብ ደረጃ ተመድቦ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ምደባ የሚካሄደው ይሰሩበት በነበረው ተመሳሳይ የአስተዳደር እርከን ይሆናል ፡፡

2/ የተሿሚዎች የትዳር አጋር በማንኛውም ጊዜ በጀት ያለው ክፍት የስራ መደብ አስካለ ድረስ የጋብቻ ማስረጃው በማህደራቸው ከተያያዘ 6 ወርና በላይ መሆኑን በማረጋገጥ በምልመላ መረጣ አቻ ማዛወሪያ የስራ ደረጃ መሰረት ተሿሚዎች በሚሰሩበት የስራ ቦታ አቅራቢያ ቀበሌ ተመድበው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

3/ በመንግስት ድጋፍ አድራጊነት የትምህርት ማሻሻያ ተልከው ትምህርታቸውን አጠናቀው ወይም በቋሚነት አቋርጠው የሚመለሱ የቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ወደ ትምህርት

ከመሄዳቸው በፊት በመደበኛ ዝውውር በቋሚነት ተመድበው ይሰሩበት የነበረው ቀበሌ ክፍት ሆኖ እንዲቆያቸው በማድረግ በነበሩበት ቀበሌ እንዲመደቡ ይደረጋል ፡፡

## 12. የወረዳዎች አመዳደብና ነጥብ አሰጣጥ

1/ ከዞን ዞንም ሆነ ከወረዳ ወረዳ ለሚደረገው ዝውውር የሚያገለግል የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ

ሀ) ምድብ አንድ

- ✓ የክልሉን ርእሰ ከተማ ባህርዳርን ጨምሮ ሌሎች የዞን ከተሞች

ለ) .ምድብ ሁለት

- ✓ የገንዳ ውኃ እና የዋግህምራ ዞን ርእሰ ከተማ ጨምሮ ከዞን ከተሞች ውጭ የሆኑ ሌሎች ወረዳዎች

ሐ) ምድብ ሶስት

- ✓ በረኸት፣ ጃን አሞራ፣ መሃል ሳይንት፣ አርጎባ፣ ዳውንት፣ ፣ ዳዋ ሃርዌ፤ ሚዳ ወረሞ፤ ቀወት ፣ ጅሌ ጥሙጋ፣

መ) ምድብ አራት

- ✓ በየዳ፣ ጠለምት፣ ዳህና ፣ ግሸራቤል

ሠ) ምድብ አምስት

- ✓ ቋራ፣ ጃዊ፣ ታች አርማጭሆ፣ ጠገዴ፤ አድአርቃይ ፤ አበርገሌ

ረ) ምድብ ስድስት

- ✓ መተማ ፣ ምዕ/አርማጭሆ ፣ አብደራፊ ከተማ አስተደደር ፣ አብርሀጅራ ከተማ አስተደደር ፣ዝቋላ ፣ ሰሃላ፣ ምዕ/በለሳ ወረዳ

2/ የስራ ቦታ ምድብ ደረጃ ነጥብ አሰጣጥ

ሀ) በምድብ አንድ ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.0 ይሆናል፡፡

ለ) በምድብ ሁለት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.1 ይሆናል፡፡

ሐ) በምድብ ሶስት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.2 ይሆናል፡፡

መ) በምድብ አራት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.3 ይሆናል፡፡

ሠ) በምድብ አምስት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.4 ይሆናል፡፡

ረ) በምድብ ስድስት ለሰራበት አንድ አመት አገልግሎት የሚሰጠው ነጥብ 1.5 ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

### 13. የዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

1/ ዝውውር የሚካተቱ/የሚፈልጉ ባለሙያዎች የዝውውር ፎርሙ በቀበሌ ደረጃ ከቀበሌ ቀበሌ ፣ ከወረዳ ወረዳ፣ ከዞን ዞን በተቀመጠለት ጊዜ መሞላቱን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

2/ ከወረዳ ወረዳ ዝዉዉር የሚሰራላቸዉን ዝውውር ፈላጊዎች መረጃ በወቅቱ ተሞልቶ እንዲደርሰው ክትትል ያደርጋል፣ የደረሰውን መረጃ ያደራጃል ፣ ከስራና ስለጠና መምሪያ ጋር በመሆን ዝዉዉሩን ይሰራል፡፡

3/ የዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ስራው የሚመለከተው ቡድን 2 ባለሙያና ስራና ስልጠና መምሪያ የሚወከል 1 ባለሙያ ሆነው የወረዳ ወረዳ ዝዉዉር በተቀመጠለት ጊዜና በተሰጠው የዝውውር መስፈርት ተሰርቶ ለስራና ስልጠና መምሪያ ኃላፊ/ም/ኃላፊ/ተወካይ እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡ የፀደቀውን በማስታወቂያ ሰሌዳ ያሳውቃል፣ በተሰራዉ ዝዉዉር ቅሬታ ያላቸውን ባለሙያዎች ይቀበላል፣ ማስተካከያ ካለ በማስተካከል ለወረዳ ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት ጽ/ቤት በደብዳቤ ያሳዉቃል፡፡

4/ ከዞን ዞን የሚዛወሩትን መረጃ አደራጅቶ ለክልል በስራና ስልጠና ቢሮ በኩል ዝውውሩእንዲሰራ መረጃ ይልካል፡፡

### 14. የወረዳ ሲቪል ሰርቪስና የሠዉ ኃብት ልማት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የመደበኛ ዝውውር ማስታወቂያ ለሁሉም የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ እንዲደርስና አመች በሆኑ ቦታ እንዲለጠፍ ማድረግና በደብዳቤ ማሳወቅ፣

2/ የገጠር ቀበሌ የስራ እድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ የዝዉዉር ፎርም በተቀመጠለት ጊዜና ፎርም መሰረት እንዲሞላ፣ እንዲደራጅና ለዝዉወር ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

3/ ከቀበሌ ቀበሌ ዝዉዉር የሚሰራላቸዉን ሙያተኞች መረጃቸዉ ተደራጅቶ እንዲመጣ በማድረግ ከስራና ስልጠና ጽ/ቤት በኃላፊ የሚወከል 1 ባለሙያ ጋር በመሆን መረጃ ያጣራል ዝውውሩን ይሰራል፣ የተሰራዉ ዝዉዉር በስራና ስልጠና ጽ/ቤት በኩል ማፀደቅና ግልጽ በሆነ ቦታ ይለጠፋል፣ የቅሬታ ማቅረቢያ ስርዓቱን ተከትሎ በተሰራዉ ዝዉዉር ቅሬታን ተቀብሎ ያስተናግዳል፡፡ ከቅሬታው ምላሽ በኃላ ዝዉዉር ለተዛወሩ ሙያተኞች የምደባ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡

4/ በወረዳው ተመልምለው ትምህርት አጠናቀው የተመለሱ፣ አዲስ የተቀጠሩ ፣ ከመደበኛ ዝውውር በኃላ የሚመጡ፣ በተለያየ ምክንያት ለሚዛወሩየገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት

ባለሙያዎችበተገኘው ክፍት ቀበሌ በጊዜያዊነት ምደባ የሚሰጥ ሲሆን በጊዜያዊ የተመደቡ ባለሙያዎች መደበኛ ዝውውር ሲሰራ በሚመጥናቸው ቦታ ሞልተው እንዲዛወሩ ያደርጋል፡፡

5/ ከመደበኛ ዝዉዉሩ ጊዜ ዉጪ በጤና እና በኑሮ የደህንነት ችግር ምክንያት ከቀበሌ ቀበሌ ተነስተዉ የሚመደቡ ሲያጋጥም ጊዜያዊ ምደባ ያደርጋል፡፡

## 15. የስራና ስልጠና ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

1/ ከዞን ዞን ዝዉዉር የሚሰራላቸዉን በወቅቱ መረጃቸዉን እንዲደራጁ ያደርጋል፣ ከዞን ዞን ዝዉዉር ይፈጽማል፡፡ ዘርፉን ለሚመራዉ ኃላፊ ያጸድቃል በማስታወቂያ ሰሌዳ ለተወዳዳሪዎች ያሳውቃል ፣በተሰራዉ ዝዉዉር ቅሬታ ካለ ተቀብሎ በቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት ያስተናግዳል፣ የመጨረሻዉን የዝዉዉር ውጤት ለዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሀብት ልማት መምሪያና ለስራና ስልጠና መምሪያ በደብዳቤ ያሳዉቃል፡፡

2/ በዞን ደረጃ የወረዳ ወረዳ ዝዉዉር በተቀመጠዉ ጊዜና መስፈርት መሰረት እንዲፈጸም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3/ ከዞን ዞን ከትምህርት መልስ እና በህግ ከለላ ምክንያት መመደብ ሲያስፈልግ ምደባ ይሰጣል፡፡

## 16. የስራና ስልጠና መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት

1/ ከወረዳ ወረዳ ዝዉዉር የሚሰራላቸዉን በወቅቱ መረጃቸዉ እንዲላክ በማድረግ የወረዳ ወረዳ ዝዉዉርን ከሲብል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ ጋር 1 በኃላፊ የሚወከል ባለሙያ በመላክ እንዲፈጸም ያደርጋል፣ ለስራና ስልጠና መምሪያ ኃላፊ/ተወካይ ቀርቦ ይፀድቃል፣ የተሰራው ዝውውር ለተወዳዳሪዎች ውጤቱ በማስታወቂያ ሰሌዳ እንዲገለጽ ያደርጋል፣ በተሰራዉ ዝዉዉር ቅሬታ ያላቸዉ ባለሙያዎች በቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት መሰረት ያስተናግዳል፣ ሂደቱን ይከታተላል፣ ከዞን ዞን ለመዛወር የሞሉትን ፎርም መረጃዉን በማደራጀት ለክልሉ ስራና ስልጠና ቢሮ በወቅቱ ይልካል፡፡የወረዳ ወረዳ ዝውውር ለተሰራላቸው የጸደቀዉን ዝዉዉር በሲ/ሰ/የሰ/ሃ/ልማት መምሪያ በኩል ለወረዳ ሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት በደብዳቤ እንዲወርድ ያደርጋል፡፡

2/ በወረዳ ደረጃ የቀበሌ ቀበሌ ዝዉዉር በተቀመጠዉ ጊዜና መስፈርት አግባብ እንዲፈጸም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3/ ከክልሉ የሚላክለትን ጨምሮ ከወረዳ ወረዳ ከትምህርት መልስ እና በህግ ከለላ ምክንያት ምክንያት ወደ ወረዳ እንዲመደቡ የተወሰነላቸውን በሲቪል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት መምሪያ በኩል ምደባ እንዲደረግላቸዉ ክትትል ያደርጋል፡፡

## 17. የስራና ስልጠና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት፡-

1/ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎችን የስራ አፈጻጸም ውጤት በየወቅቱ እየሞላ ለሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እንዲደርስ ያደርጋል። በወቅቱ ከሠራተኞች ማህደር ጋር መያያዙን ይከታተላል።

2/ የገጠር ቀበሌ የስራ እድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ የዝዉዉር ፎርም በተቀመጠለት ጊዜና ፎርም መሰረት እንዲሞላ፣ እንዲደራጅና ለዝዉወር ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋል።

3/ ከቀበሌ ቀበሌ ዝዉዉር የሚሰራላቸዉን ሙያተኞች መረጃቸዉን ያደራጃል፣ ከሲቨል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ጋር በመሆን ዝዉዉሩን ይሰራል፣ ለጽ/ቤት ኃላፊው ያፀድቃል፣በማስታወቂያ ሰሌዳ ያሳውቃል፣ በተሰራዉ ዝዉዉር የሚቀርቡ ቅሬታዎች ካጋጠሙ በአግባቡ በቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት ምላሽ ይሰጣል፣በመጨረሻው የዝዉዉር ዉጤት መሰረት ለተዛወሩ ሙያተኞች በሲቨል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት በኩል የምደባ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ያደርጋል ፣ በተመደቡበት ቀበሌ ሙያተኛ መድቦ የስራ ርክክብ እንዲደረግ ያደርጋል፣

4/ በወረዳ ተመልምለው ለትምህርት የተላኩ ትምርታቸዉን አጠናቀዉ የተመለሱ ወይም በቋሚነት ትምህርታቸውን አቋርጠው የተመለሱ የገጠር ቀበሌ የስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎችን ሲመለሱ እንዲመደቡ ለሲቨል ሰርቪስና የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት መረጃ ይልካል፣

5/ ከመደበኛ ዝዉዉሩ ጊዜ ዉጪ በጤና እና በኑሮ የደህንነት ችግር ምክንያት ከአንድ ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ተነስተዉ የሚመደቡ ሲያጋጥም ጊዜያዊ ምደባ እንዲሰጥለት ለሲቨል ሰርቪስና ለሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ክፍት ቀበሌዎችን ያሳውቃል፣

6/ በየሁለት አመቱ ለሚሰራው ዝውውር በወረዳው ውስጥ ያሉ የገጠር ቀበሌዎችን ባላቸው የስራ አመችነት፣ የገጠር መሰረተ ልማትና የአየር ንብረት ሁኔታ እንዲሁም ሌሎች ሁኔታዎችን በማየት ሁሉንም በቅደም ተከተል ደረጃቸውን ማውጣትና ከገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ጋር የጋራ ውይይት በማድረግስምምነቱን ለወረዳው ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል።

7/ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ወደ ተዛወሩበት ቀበሌ ከመሄዳቸው በፊት በቦታው ተገኝቶ የሰነድና የስራ ርክክብ በአግባቡ መፈጸሙንና የርክክብ ሰነድ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

## 18. የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

1/ የሚቀርብለትን የዝውውር ፎርም በጊዜ ገደቡ መሰረት በትክክል ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ዝውውሩ ከመሰራቱ በፊት የመረጃ ስህተት ያለበት ወይም የዝውውር ፎርም መቀየር ካስፈለገ የዝውውር መሙያ ጊዜ ሳያልፍ በማመልከቻ በወረዳዉ ስራና ስልጠና ጽ/ቤት በኩል አስመርቶ ለወረዳው ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤት ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡

3/ ማንኛዉን የገጠር ስራ እደል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ዝዉዉር ከተሰራ በኃላ ዝውውሩን መሰረዝ አይችልም፡፡

4/ የዝውውር ደብዳቤ የደረሳቸው ሁሉም የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ደብዳቤው በደረሳቸው በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ በእጃቸው ያሉ ዝርዝር መረጃዎችን ወይም የተሰሩ ስራዎችን፣ፋይሎችንና ንብረቶችን የቀበሌው ሊቀመንበር ወይም ስራ አስኪያጅ ባለበት በአዲስ ተዛዉሮ ለተመደበዉ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ ርክክብ በመፈፀም አዲስ ወደ ተመደቡበት የገጠር ቀበሌ በመሄድ ሥራ እንዲ ጀምሩ ይደረጋል፡፡ሙያተኛ ያልተመደበበት ቀበሌ ከሆነ ለቀበሌዉ ሊቀመንበር በጊዜያዊነት ያስረክባል፡፡

## 19. በየደረጃው ዝዉዉር የሚሰሩ የኮሚቴ አባላት አደረጃጀት፡-

1/ በክልል ደረጃ፡-

- የስራና ስልጠና ቢሮ......የሠዉ ኃብት አስተ/ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር..... ሰብሳቢ
- የስራና ስልጠና ቢሮ...የሠዉ ኃብት አስተ/ዳይሬክቶሬት አንድ ባለሙያ....አባልና ጸሃፊ
- የስራና ስልጠና ቢሮ ......የስራ እድል ፈ/ኢን/ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር......አባል

2/ በዞን ደረጃ፡-

- የሲ/ሰ/የሰ/ሃብት ልማት መምሪያ ....የሠዉ ኃብት አስተዳደር ቡድን መሪ..... ሰብሳቢ
- የሲ/ሰ/የሰ/ሃብት ልማት መምሪያ የሠዉ ኃብት አስ/ አንድ ባለሙያ.....አባልና ጸሀፊ
- የስራና ስልጠና መምሪያ.......... የስራ ዕድል ፈ/ኢንተ/ልማት ቡድን መሪ ------አባል

3/ በወረዳ ደረጃ፡-

- የሲ/ሰ/የሠ/ኃብት ልማት ጽ/ቤት ...የሠዉ ኃብት አስተዳደር ቡድን መሪ..... ሰብሳቢ
- የሲ/ሰ/የሠ/ኃብት ልማት ጽ/ቤት ....የሠዉ ኃብት አስተ/ አንድ ባለሙያ.አባልና ጸሀፊ
- የስራና ስልጠና ጽ/ቤት .......... የስራ እድል ፈ/ኢን/ልማት ቡድን መሪ....አባል

## ክፍል አራት

## መደበኛ ዝውውር የሚፈፀምበት ወቅት፡-

### 20. የዝውውር ፎርም መሙያ ወቅት፡-

1/ ከቀበሌ ቀበሌ፣ ከወረዳ ወረዳና ከዞን ዞን የዝውውር ፎርም የሚሞላበት ጊዜ ከየካቲት 10 እስከ የካቲት 30 ባሉት የስራ ቀናት ዉስጥ ይሆናል፡፡

2/ የተሞላው የዝውውር ፎርም ከመጋቢት 1 እስከ መጋቢት 5 ባሉት የስራ ቀናት ለስራና ስልጠና ጽ/ቤትና ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡የተሞላው የዝውውር ፎርም ከመጋቢት 6 እስከ መጋቢት 14 ድረስ ስለትክክለኛነቱ ተረጋግጦና ቅሬታ ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ ይጠናቀቃል፡፡

3/ ከወረዳ ወረዳ የዝውውር ፎርም የሞሉት መረጃ ከመጋቢት 15 እስከ መጋቢት 20 ባሉት የስራ ቀናት ለስራና ስልጠና መምሪያና ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ይደርሳል፡፡

4/ ከዞን ዞን የዝውውር ፎርም የሞሉት መረጃ ከመጋቢት 21 እስከ መጋቢት 25 ባሉት ስራ ቀናት ለክልል ስራና ስልጠና ቢሮ ይደርሳል፡፡

### 21. የዝውውር መፈፀሚያ ወቅት

1/ የዞን ዞን ዝውውር የሚሰራበት ጊዜ ከሚያዚያ 10 እስከ ሚያዚያ 20 ባሉት የስራ ቀናት ተሰርቶ እስከ ሚያዚያ 25 ዝርዝሩ ለዞን ይላካል፤ ከሚያዚያ 26 እስከ ግንቦት 15 ድረስ ባሉት የስራ ቀናት ቅሬታ ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ ይጠናቀቃል፡፡

2/ ከወረዳ ወረዳ ለመዛወር የሞሉትና በክልል ደረጃ ተወዳድረው ከዞን ዞን የተዛወሩት በስራና ስልጠና መምሪያና ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ዝውውር ከግንቦት 16 እስከ እስከ ግንቦት 22 ባሉት የስራ ቀናት ተሰርቶ ለስራና ስልጠና ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ከግንቦት 23 እስከ ሰኔ 10 ድረስ ቅሬታ ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ ይጠናቀቃል፡፡

3/ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ከቀበሌ ቀበሌ ዝውውር የሚሰራበት ጊዜ ከሰኔ 11 እስከ ሰኔ 15 ባሉት የስራ ቀናት ዝውውሩ ተሰርቶ በየቀበሌው እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ ከሰኔ 16 እስከ ሰኔ 24 ባሉት የስራ ቀናት ቅሬታ ተሰምቶ ውሳኔ ተሰጥቶ ይጠናቀቃል፡፡

4/ የተዛወሩ ሙያተኞች የስራና የንብረት ርክክብ የሚደርጉበት ከሰኔ 25 እስከ ሰኔ 30 ባሉት የስራ ቀናት ይሆናል፡፡

5/ ዝውውር የተሰራላቸው ሙያተኞች በተመደቡበት ቀበሌ ስራ የሚጀምሩበት ከሀምሌ 1 እስከ ሀምሌ 5 ባሉት የስራ ቀናት ስራዎችን ተረክበው መጀመር ይጠበቅባቸዋል፡፡

6/ አንድ ጊዜ ተሞልቶ የቀረበ የዝውውር ፎርም የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል አምስት.

### 22. የተጠያቂነት ወሰን

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት የዝውውር ወቅቱን ጠብቆ የዝውውር ፎርም በወቅቱ ያላወረደ፣ ፎርሙን ያላስሞላ፣ መረጃውን በወቅቱ ያልሰበሰበ፣ ለሚመለከተው ያላቀረበ የስራና ስልጠና ጽ/ቤት ኃላፊ/ም/ኃላፊ/ ተወካይ ለሚደርሰው የሰራተኞች አስተዳደራዊ በደል አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2/ በስራና ስልጠና ጽ/ቤት የሚፈጠረው ችግር እንዳለ ሆኖ የዝውውር ፎርም መሙያ ወቅት ዝውውር ያልሞላ የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ለሚፈጠረው የዝውውር ቅሬታ እራሱ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

3/ ማንኛውም የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች ሕጋዊ ባልሆነ ወይም በተጭበረበረ ወይም በሐሰተኛ የስራ ልምድ ወይም ጋብቻ ወይም የሕክምና ወይም የማህበራዊ ችግር ማስረጃ ወይም በሌላህገ-ወጥ ምክንያት እንዲዛወር ያደረገ ወይም ለመዛወር ማስረጃ እንዲያዝለት ያቀረበ ባለሙያ አግባብ ባለው የወንጀልና የአስተዳደራዊ ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4/ ይህን መመሪያ በተዛባ መንገድ የፈፀመ ወይም ማስረጃ ሳያቀርብ እንደቀረበ አድርጎ ዝውውር የፈፀመ ወይም ያስፈፀመ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ አግባብ ባለው የወንጀልና የአስተዳደራዊ ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5/ በየደረጃው ተሞልቶ ለሚመለከታቸው አካላት በሚላከው የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎች የግል መረጃ ላይ አላግባብ ተሞልቶ ለሚፈፀመው ችግር መረጃውን የሞላው ባለሙያ ወይም ያረጋገጠው የስራ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

6/ የዝዉዉር ተጠቃሚ የሆነ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ በተመደበበት ቀበሌ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ስራ መጀመር ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

### 23. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1/ ማንኛውም በዝውውሩቅሬታ ያለውና አስተዳደራዊ በደል ተፈጽሞብኛል የሚል የገጠር ቀበሌ ስራ ዕድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያ መደበኛውን የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት ተከትሎ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ጥናት ባለሙያዎችን ዝዉዉር በተመለከተ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ አዳዲስ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በስራና ስልጠና ቢሮ አቅራቢነት የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አይቶ አስፈላጊ አንቀጾችን የመጨመርና የማዉረድ ስልጣን አለዉ፡፡

3/ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈነ የነጥብ አሰጣጥና የውጤት አያያዝ እና ሌሎች ጉዳዮችበሲቪል ሰርቪስና የሠዉ ኃብት ልማት ኮሚሽን ባወጣው ምልመላና መረጣ መመሪያ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

4/ ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛዉም ጊዜ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን ሊሻሽለው ይችላል፡፡

5/ ዝውውሩ በሚሞላበት ጊዜ አገልግሎት የሚታሰበው እስከ ሰኔ 30 ድረስ ያለው አገልግሎታቸው ነው፡፡

### 24. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ፀድቆ ወጭ ከሆነበት 24/12/2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ ከመመሪያው ጋር በተያያዘ የሚነሳ መብትና ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትሕ ቢሮ ተመዝግቦ በሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**ወ/ሮ ባንቻምላክ ገ/ማርያም**

**የአ ብክመ ሲ/ሰ/ና የሰ/ሀ/ልማት**

**ኮሚሽን ኮሚሽነር**

ቅፅ-1

**በአንድ ወረዳ ከቀበሌ ቀበሌ ለሚደረግ ዝውውር የዝውውር መሙያ ቅጽ**

ቀበሌ ---------------------------------

| ተ.ቁ | ስም ከነ አያት | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት ሙያ | የቅጥር ዘመን ቀን/ወር/ዓ.ም | የሙያ ስያሜ ደረጃና ደመወዝ | አሁን ከለበት ቀበሌ የተመደበበት ቀን/ወር/ዓ.ም | የስራ ተኛው አገልግሎት ቀን/ወር/ዓ.ም | የትዳር አጋር አገልግሎት ቀን/ወር/ዓ.ም | ጠቅላይ አገልግሎት ቀን/ወር/ዓ.ም | ባለትዳር ከሆኑ የትዳር ጓደኞቻቸው የሚኖሩበት/ የሚሰሩበት | | ለመዛወር የሚፈልጉበት ቀበሌበቅደም ተከተል | | | እየሰሩ ያሉበት ቀበሌ የተሰጠው ምድብ ደረጃ | የሞላው ሰራተኛ ፊርማ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | ወረዳ | መ/ቤት | 1 | 2 | 3 | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ቅፁን ያስሞላው ባለሙያ ሙሉ ስም-----------------------

የስራ ድርሻ------------------------

ቀን----------------------

ፊርማ-------------------

ያፀደቀዉ ሃላፊ ስም-------------------

የስራ ድርሻ--------------------------

ቀን--------------------------------

ፊርማ----------------------------

ቅጽ-2

**በአንድ ዞን ከወረዳ ወደ ወረዳ የዝውውር መሙያ ቅጽ**

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት ሙያ | የቅጥር ዘመን ቀን/ወር/ዓም | የሙያ ስያሜ ደረጃና ደመወዝ | የስራተኛቀው አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | የትዳር አጋር አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | አማካይ አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | ባለትዳር ከሆኑ የትዳር ጓደኞቻቸው የሚኖሩበት/ የሚሰሩበት | | ባለሙያዉ የሚሰራበት ቀበሌ የተሰጠው ምድብ ደረጃ | ለመዛወር የሚፈልጉበት ወረዳ በቅደም ተከተል | | | የባለሙያው ስልክ ቁጥር | ዝውውሩን ያሞላው ሰራተኛ ፊርማ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | ወረዳ | መ/ቤ | | 1 | 2 | 3 | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ዝውውሩን ያስሞላው ባለሙያ ሙሉ ስም---------------------

የስራ ድርሻ-----------------------------------

ቀን---------------------

ፊርማ------------------

ያፀደቀዉ ሃላፊ ስም ----------------

የስራ ድርሻ------------------------

ቀን-----------------------------

ፊርማ---------------------------

ቅጽ-3

## ከዞን ዞን የዝውውር መሙያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የስለጠኑበት ሙያ | የቅጥር ዘመን ቀን/ወር/ዓም | የሙያ ስያሜ ደረጃና ደመወዝ | የስራተኛቀው አገልግሎት አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | የትዳር አጋር አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | አማካይ አገልግሎት ቀን/ወር/ዓም | ባለትዳር ከሆኑ የትዳር ጓደኞቻቸው የሚኖሩበት/ የሚሰሩበት | | ባለሙያዉ የሚሰራበት ወረዳና የወረዳ ምድብ ደረጃ | ለመዛወር የሚፈልጉበት ዞን በቅደም ተከተል | | | የባለሙያው ስልክ ቁጥር | ዝውውሩን ያሞላው ሰራተኛ ፊርማ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | ወረዳ | መ/ቤ | | 1 | 2 | 3 | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ዝውውሩን ያስሞላው ባለሙያ ሙሉ ስም----------------------

የስራ ድርሻ-----------------------------------

ቀን---------------------

ፊርማ------------------

ያፀደቀዉ ሃላፊ ስም ----------------

የስራ ድርሻ-------------------------

ቀን-----------------------------

ፊርማ---------------------------